# የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ዛሬም እንደ ትናንት...

**ከሃብሮሜዬ,** 06/30/09

በዓለም ደሞክራሲ፤ ሰላም፤ልማትና መልካም አስተዳደርን የሚዬፈልግ ህዝብ አለ ብሎ መናገር የሚያስደፍር አይደለም፡፡ምክንያቱ ህዝቦች አገራቸው ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባትና ለኑሯቸው ምቹ እንደትሆን ሁሌም ይመኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከህዝብ ፍላጎት በላይ የራሳቸውን ፍላጎት የሚያስቀድሙ ጸረ ደሞክራሲ አስተሳሰብ ያላቸው አምባገነን መሪዎች የህዝብን አስተሳሰብ በመጨፍለቅ ዜጎቻቸውን ለደህነትና ለስደት ይዳርጋሉ፤ አልፎ ተርፎም አገሪቱ ወደ እርስ በርስ ጦርነትና እልቂት እንደትገባ በር ይከፍታሉ፡፡እነዚህ መሪዎች የሃገራቸውን የወስጥ ችግር ለመሸፈን በጎረቤት ሃገሮች ጉዳይ ጣልቃ በማባት የሕዝባቸውን የትኩረት አቅጣጫ ለማዞር ይሞክራሉ፡፡ህዝቡም ያለፍላጎቱ በሃይል አስገድደው በጦርነት ወስጥ እንዲማግድ በማድረግ ሽንፈትን ቢከናነቡም በእብሪት ተወጥረው ራሳቸውን እንደ አሸናፊ አድርገው በመቁጠር ከስህተታቸው ሊማሩ አይፈቅዱም ፡፡ከመጀመሪያውንም መሰረታቸው ህዝብ አይደለምና !

ይህን ለማለት ያነሳሳኝ የዛሬ አስራ አንድ ዓመት ግደም የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ የፈጸመውን ወረራ ለማስታወስ ያህል ነው፡፡የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች በደሞክራሲያዊ ምርጫ ወደ ስልጣን ያልመጡ ህዝባዊ መሰረት የሌላቸው አምባገነን ስርዓቶች መብታቸው ሲረገጥና ክፉኛ እንዲሰቃዩ ማድረጋቸው የቅርብ ጊዜ ትወስታ ነው፡፡ይህንን የስቃይ ቀንበር በላይ በላያቸው ሲጫኑ ለሸከሙት ወደማይችሉበት ደረጃ በመድረሱ መራራ ህዝባዊ ትግል አካሂደው በሰራዊትና በዘመናዊ መሳርያ ብዙት አፍሪካ ወደር የሚዬገኝለት ደርግ ለመደምሰስ ችለዋል፡፡

ይሁን እንጂ የኤርትራ መንግስት ስልጣኑ ሲጨበጥ ክቡር ሂወቱን ከፍሎና አካሉን ጎድሎ ወደዚህ ደረጃ ያመጣውን የኤርትራ ህዝብ ፀሐይ ሳትጠልቅ ነው የረሳው፡፡

የሕዝቡ ጥያቄ የነበረውን ልማት ለማፋጠን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከማውጣት ይልቅ ወጣቶችን በሃይል ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ እንዲሄዱ ማድረጉን ተያያዘው፡፡ በአንጻሩ የኢትዮጵያ መንግስት የህዝቡን ዋነኛና መሰረታዊ ጥያቄዎች የነበሩት ልማት፤ደሞክራሲና ሰላም ለማስፈን ሲል የነበረውን ሰራዊት በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስና ፊቱን ወደ ልማት እንዲያዞር በማድረግ፤በህዝብ ተሳትፎ የተመሰረተ የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ መንግስት በማፅደቅ፤ የዜጎች ሰብአዊና ደሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ አደረገ፡፡እንዲህም ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በማሳት ፖሊሲና ስትራተጂ በመቅረጽ ወደ ተግባር ተሸጋገረ፡፡

ይህ የኢትዮጵያ የልማት አቅጣጫ ያልተዋጠለት ጥገኛው የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ተንጠልጥሎ ለመኖር ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡የአገሪቱ የገበያ ስፋት ሲሰላ ታሳቢ ያደረገው የኤርትራ ህዝብ ብዛት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብም በመደመር በተሳሳተ ፖሊሲወና ስትራተጂው ሕብረተሰቡን በሐሰት በመደለል የቁም ቅዠት ወስጥ ከተተው፡፡ በመጨው ጥቂት ዓመታትም ኤርትራ በኢኮኖሚ እንደ "ሲንጋፖር" በወታደራዊ ሃይል እንደ "እስራኤል" እንደምትሆን ጭምርም ለህዝቡ ይሰብክ ጀመር፡፡እንደ ሲንጋፖር ለመሆን መመኘት ጥሩ ቢሆንም ታሳቢ ያደረገው ግን የኤርትራ ኢኮኖሚ ሳይሆን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተንጠልጥሎ ያለአግባብ ለመክበር ነበር፡፡በሱም አላበቃም በወታደራዊ ብቃትም የምስራቅ አፍሪካ አወራ ለመሆን ትልቅ ህልምም ነበረው፡፡

ይህን የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ መንጥልጠልና ጥገኛ መሆን እንደማይቻል ሲያረጋግጥለት "ሲንጋፖር"የመሆን ህልሙን ክፉኛ ተናጋ፡፡ይህ ሕልሙ አለመሳካቱ ሲገነዘብ የቀረችውን የቅዠት ህልሙን ለማስጠበቅ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመድፈር ፤ የምስራቅ አፍሪካ አወራ ለመሆን የነበረውን ህልም ማሳካት!

መሰረቱ ህዝብ የሆነ መንግስት በቂ የሆነ የመከላከያ ሃይል ባልነበረው ጊዜም ህዝቡ በፍላጎቱ በነቂስ በመውጣት እብሪተኛውን የኤርትራ መንግስት ሽንፈት ተከናንቦ እንዲሄድ አድርገዋል፡፡ሻዕብያ የተመኛቸውን ሁለት ታላላቅ ህልሞች ከሰማይ ወተት እንደ ማለብ መሆናቸውን ሲገነዘብ ተስፋ ቆርጦ የህዝቡን ጉዳይ እንደ ቁብ ሳይቆጥር እንደርሱ ዓይነት ቀቢጸ ተስፋ የሽብር ቡድኖች በማስባሰብ ላይ ተጠመደ፡፡የኤርትራ ህዝቡም ከእለት ወደ እለት የስቃይ ህይወት እንዲገፋ ተደረገ፡፡ አሁንም በአምባገነኑ መንግስት ክፉኛ እየተሰቃየ ነው፡፡

የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ጋር ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት ስላልነበራቸው የአምባገነኑ የኤርትራ ስርዓት ጭቆና መሸከም ሲያቅታቸውስደት እጣ ፈንታቸው ሆነ፡፡ ሃገራችንም እነዚህን ዜጎች በመልካም ጉርብትና ተቀበለቻቸው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስትም በአስከፊው የኤርትራ መንግስት ጭቆና ምክንያት ከአገራቸው የተፈናቀሉ ኤርትራውያን በአግባቡ በመቀበልና በማስተናገድ ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ በሽመልባና በማይዓይኒ የሚገኙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኤርትራውያን የኢትዮጵያ መንግስት ባለው ዓቅም የተለያዩ ድጋፎች እያደረገላቸው ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር በኢትዮጵያ መኖር የሚፈጡ ኤርትራውያን የመኖርያ ፍቃድ እንዲያገኙ በማድረግና በግል ኮሌጆችም ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ዕድል ተሰጥቷቸዋል፡፡ቀላል የማይባሉ ኤርትራውያንም በዚህ ዕድል ተጠቃሚ እየሆኑ ናቸው፡፡
ወደ ወጭ አገር መሄድ የሚፈልጉም የኢትዮጵያ መንግስት ከሚመለከታቸው አገሮችና ድርጅቶች በመነጋገር ወደ ፈለጉት አገር እንዲሄዱ ያልተቆጠበ ጥረት እያደረገ ነው፡፡በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ወደ ሚፈልጉት አገር ሄደዋል፡፡

የኤርትራ መንግስት በአገራችን ላይ በፈጸመው ወረራ ምክንያት ለብሄራዊ ደህንነታችን ስጋት ይሆናሉ ተብለው የተጠረጠሩ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኤርትራውያን ከሃገር እንዲወጡ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ እነዚህ ኤርትራውያን ከሃገራችን ሲወጡ ያላቸውን ሃብት አንዳንዶቹ ለወኪሎቻቸው በማስጠት፤አንዳንዶቹ በቂ ጊዜ አግኝተው ያፈሩትን ሃብት ሸጠው ፤የቀሩትን ደግሞ መንግስት በወኪልና እንዲያስተዳድርላቸው በማድረግ ነው፡፡

የኤርትራ መንግስት ባወጀበን ጦርነትና በፈጸመበን ወረራ ምክንያት ለአገራችን ደህንነት ሲባል ከሃገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራውያን በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ለብሔራዊ ደህንነታችን ስጋት ይሆናሉ የተባሉትና ከሃገር እንዲወጡ የተደረጉት ኤርትራውያን በተፈጠረው አስተማማኝ ሰላም ንብረታቸውን እንዲወስዱ ለማስቻል መንግስት መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

ይህን መመርያ መውጣቱ ትክክል ነው ወይስ አይደለም ብለን ማምግሙ ተገቢ ነው፡፡በመጀመርያ ደረጃ መንግስት ከአገሪቱ እንዲወጡ ያደረጋቸው ኤርትራውያን ለአገሪቱ ደህንነት ሲል እንጂ በላባቸው ጥረው ግረው ያካበቱትን ሃብት ለመዝረፍ እንዳልሆነና መንግስትም መቼውም ቢሆን የግለሰብ ንብረቶችን የመውረስ ዓላማ እንደሌለው በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡ አምባገነኑ የኤርትራ መንግስት ከኢትዮጵያ የወጡ ኤርትራውያን የኢትዮጵያ መንግስት ንብረታችሁን ዘርፏል ብሎ የተለመደው ሃሰተኛ ፕሮፓጋንዳው ሲያላዝን ከርሟል፡፡ለነገሩ ሻዕብያ በማዋሸትና ያልሆነውን ሆነ በማለል የኤርትራ ህዝብ እንደ እምባሶይራ ተራራ አይደል የሚያውቀው!

መመሪያውን የሚመለከታቸው ኤርትራውያን ወደ አገራችን ተመልሰው ኢንቨስት የሚያደርጉ ከሆነ አሁንም ለደህንነታችን ስጋት ሊሆኑ አይችሉም ወይ የሚል አንዳንድ ስጋቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡እኔም በመጀመሪያ ስለ መመርያው ስሰማ ብልጭ ያለኝ ጥያቄ ይሄ ስለነበር፡፡

በተለይ ኤርትራውያኑ በኢንቨስትመንት ሲሰሙ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 አንቀጽ 2(5) መሰረት በሃገራችን ወስጥ እንደ ሃገር ወስጥ ባለሃብት ሆነው እንደሚቆጠሩ ስሰማ ግራ ተጋብቼ ነበር፡፡ማድረግ ያለብኝ ነገር ካለ የአገር ወስጥ ባለሃብት ማለት ምን ማለት እንደሆነና መመሪያው የሚመለከታቸውን ኤርትራውያን የትኞቹ እንደሆኑ ማረጋገጥ ነው፡፡

የኢንቨስትመንት አዋጁ እንደሚገልጸው የአገር ወስጥ ባለሃብት ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በስራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ወስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን፤መንግስትንና የመንግስት ልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ አገር ወስጥ ባለሃብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ሃገር ዜጋን እንደሚጨምር ነው የሚገልጸው፡፡

ይህ የኢንቨስትመንት አዋጅ የውጭ አገር ዜጎች እንደ አገር ወስጥ ባለሃብቶች ሆነው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሃገሪቱን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማስደግና ለማስፋፋት ይረዳል፡፡እነዚህ የአገር ወስጥ ባለሃብቶች በሁለት ይከፈላሉ፤እነሱም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶችና የውጭ ዜግነት

ያላቸው ባለሃብቶች ናቸው፡፡እንደ አገር ወስጥ ባለሃብቶች ሆነው የሚሰሩ የወጭ ዜጎች እንደ ኢትዮጵያዊ ባለሃብት እኩል ይታያሉ ማለት ግን አይደለም፡፡እነዚህን ባለሃብቶች እንደ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶች በባንክ፤በቴሌኮምዩኒኬሽን፤በሲቪል አቭየሽን፤በኢንሹራንስ፤በኤለክትሪክ ሃይል ...ወዘተ ላይ ኢንቨስት ሚድረግ አይችሉም፡፡ይህ ደግሞ መንግስት ለአገሪቱ ደህንነት ለማጠበቅ እያደረገ ያለወን ጥንቃቄ የሚያሳይ ነው፡፡መንግስት በዚህ ምህረት የለሽ የወድድር ዘመን ኢንቨስትመንት በአገራችን እንዴት መጨመር እንደሚቻልና ከዚህም ተያይዞ የሚመጣው የአገራችን ደህንነት ጉዳይ እንዴት አስተማማኝ ሊሆን እንደሚችል ሁለቱን አጣጥሞ እየሰራ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ፡፡

አሁን ወደ አገራችን መጥተው ኢንቨስት የሚያደርጉ ኤርትራወያንም ልክ እንደ ጅቡቲ ዜግነት ያላቸው የአገር ወስጥ ባለሃብቶች ሁሉ እነሱም ኤርትራዊ ዜግነት ያላቸው የአገር ወስጥ ኢንቨስተሮች ስለሚሆኑ ከአገር ደህንነት አኳያ ስጋት ሊኖር አይችልም፡፡ለሁሉም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራወያን መመሪያው እኩል ተጠቃሚ አያደርግም፡፡የኤርትራ መንግስት በተለየ ሁኔታ ከሚደራቸው የንግድ እንዲሁም የፀጥታ ተቋማት ጋር የቅርብ ትስስር ባላቸው ኤርትራወያን ላይ አይሆንም፡፡ በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክቱ ከሃገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራወያን ጉዳይ ከጦርነቱ በፊትና በኋላ በኤርትራ ወይም በሌሎች አገሮች ከሚገኙ የኤርትራ መንግስት ንግደና የጸጥታ ተቋማት ጋር ትስስር የሌላቸው መሆናቸው መሆናቸውን በብሔራዊ የመረጃና የደህንነት አገልግሎት በኩል እየተጣራ እንደሚወሰን ነው፡፡ይህን አፈጻፀም የሚከታተል ኮሚቴ ከወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ከገንዘብና ኢኮኖሚ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ከብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎትና ከፌደራል ፖሊስ አራት አባላት የያዘ ኮሚቴ በመመሪያው አንቀጽ 8 መሰረት ስለሚቋቋም ከአገራችን ደህንነት አኳያ ምንም አይነት ስጋት እንደሌለ ተመልክቼያለሁ፡፡

እነዚህ ከኢትዮጵያለደህንነት ስጋት ናቸው ተብለው የወጡ ኤርትራወያን ባለሃብቶች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ጀምረወት የነበሩት ኢንቨስትመንት ለማስቀጠል፤ በባንክ በዝግ ሐሳብ (account) የተቀመጠ ገንዘባቸወን አንቀሳቅሰው ሃገራችን ከተያየዘችው ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑና ለሌሎችም እንዲጠቅሙ ነው፡፡ስለሆነም እነዚህ ባለሃብቶች ወደ ስራ በመግባታቸው ምክንያት አዳስ የስራ ዕድል ሚፈጠሩ የሚዩቀር ነው፡፡ኢንቨስትመንት ባለበት ሁሉ የስራ ዕድል አብሮ ስለሜኖር፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ይህ መመሪያ አንኳር የሆኑ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው የተገነዘብኩት፡፡እንደሚታወቀው ከጎረቤት አገሮች ሁሉ በታሪክና በባህል ትስስር የጠበቀ ግንኙነት ያለን ከኤርትራ ጋር ነው፡፡ይሁን እንጂ በእብሪተኛው የኤርትራ መንግስት የማንአለብኝነት በተፈጸመብን ወረራ ምክንያት የኤርትራ ህዝብ ወዳልተፈለገ ጦርነት እንዲገባ ተገዷል፡፡ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ከኤርትራ ህዝብ ጋር ምንም ዓይነት ቁርሾ አልነበረወም፤አሁንም የለወም፡፡የኢትዮጵያ መንግስት ከመጀመሪያም የኤርትራ ህዝብና አምባገነኑን የኤርትራ መንግስት ለያይቶ ነው የሚያያቸው፡፡ምክንያቱም የኤርትራ ህዝብ እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ሰላም ወዳደና ታታሪ ህዝብ መሆኑና ጦርነት ፈላጊም አለመሆኑን ስለምገነዘብ፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይም ከጎረቤት አገሮች የሚፈረን ግንኙነት በመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ላይ የተመሰረተ መሆኑና የልማቱና የዴሞክራሲ ዓላማችንን እውን ከሚድረግ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይህን መመሪያ ከልማታችንና ደህንነታችን አኳያ ሲታይ ትክክልና ተገቢ ነው እላለሁ።

ይህን መመሪያ መውጣቱ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች መካከል የነበረውን የቆየ መልካም ጉርብትና አሁንም እንዳለና ለወደፊትም እንደሚፎር፣ግጭቱ ከጦርነት ናፋቂወና ኤርትራን የቀበጸ ተስፋ አሸባሪዎች ቡድን መናሃርያ ያደረገው አምባገነኑ የሻዕቢያ ማግስት ጋር እንደሆነ ትልቅ ማሳያ ነው።

ከዚህ ባሻገር ይህን መመሪያ መውጣቱ በዚህ ምህረት የለሽ ወድድር ያለበት የግሎባላይዜሽን ዘመን ከተለያዩ የዓለም አገሮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት በሚድረግ ላይ ያሉትና ለወደፊትም ኢንቨስት ለሚያደርጉ ሁሉ አገራችን በጥረታቸወና በላባቸው ያካበቱትን ሃብት በማንኛወም ሁኔታ ለንብረታቸው ዋስትና የምትሰጥ አገር መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ደግሞ አገራችን ለኢንቨስትመንት የተመቸችና በአጋጣሚዎች የሚይዋዥቅግልፅና ቀጥተኛ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ እንዳላት በግልጽ የሚያሳይ ነው። የውጭ ባለሃብቶችን ወደ አገራችን መጥተው ያለ ምንም ስጋት ኢንቨስት እንዲያደርጉም የሚያበረታታ ነው።

የሻዕብያ ማግስት የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለሟጨት የተለያዩ የዘቀጡ የፕሮፓጋንዳ ስልቶች ቢጠቀምም ልማቱ ፣ሰላምና ዴሞክራሲ ናፋቂው የኤርትራ ህዝብ ግን ዛሬም እንደ ትናንት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመልካም ጉርብትና፣በሚፈቃቀርና በመተሳሰብ እየኖረ ነው። ህዝብ ሁሌ ሰላም፣ልማትና ዴሞክራሲ ይፈልጋልና። ሰላም!